
# ዐውደ ንዋይ

## የላቀ አገልግሎት፣ ደስተኛ ደንበኛ!




የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia


ቅጽ 01 ቁጥር 03
ሰኔ 2017 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia



## ማውጫ

የዋና አዘጋጁ መልእክት........................................ 3
ዐበይት ክንውኖች ........................................ 4
ስኬታችን........................................ 12
የባንክ አገልግሎት ........................................ 13
መዝናኛ ........................................ 17
ከፎቶ ማኅደር ........................................ 18

ዐውደ ንዋይ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኮርፖሬት ኮምዩኒኬሽን መምሪያ በየሩብ ዓመቱ የምትታተም ዜና መጽሔት ናት።

**አድራሻ**
አዲስ አበባ ቂርቆስ ክ/ከተማ
የቤት ቁጥር፡- አዲስ
ኢሜይል፡-
AlsenAssefa@cbe.com.et

**ዋና አዘጋጅ**
አልሰን አሰፋ

**ም/ ዋና አዘጋጅ**
ብርሃኑ ኃይሉ

**ዝግጅት አስተባባሪና አርታዒ**
አስቻለው ተክሉ

**ኅትመት እና ስርጭት አስተባባሪ**
ተፈሪ ጋሞ

**ዐምድ አዘጋጆች**
ማርታ ዘሪሁን
ተመስገን ዳምጠዉ
ኦሊቃ በላይ

**የፎቶግራፍ ባለሙያ**
ዳግም ጌታቸው

**ሌይ አወት ዲዛይነር**
አስቻለ ዳኜ

በዜና መጽሔቷ በወጡ ጽሑፎች እና ምስሎች ለተገለጹ መረጃዎች፣ ሐሳቦች እና አስተያየቶች እንደ አግባቡ የጽሑፍ አቅራቢዎች ወይም ምንጮቻቸው ሓላፊነት ይወስዳሉ።

# የዋና አዘጋጁ መልእክት



*ዐውደ ንዋይ በመጀመሪያ ቅጽ የ3ኛ ክፍል ዕትም ብቅ ብላ ቀጣይነቷን አረጋግጣለች።*

*ዜና መጽሔቷ በቀደሙት ሁለት ክፍሎች እንዳደረገችው፣ በዚህ ክፍል የባንካችንን የ3ኛ ሩብ ዓመት ዐበይት ክንውኖች የተመለከቱ መረጃዎችን አቅርባለች። ባንካችን በሩብ ዓመቱ የደረሰበትን የአፈጻጸም ደረጃ በቁጥር መረጃ ደግፋ በአጭሩ ታሳያለች። በተጨማሪም በሩብ ዓመቱ በተከበረው የባንካችን የደንበኞች አገልግሎት ወር ዙሪያ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የካስተመር ኤክስፒሪየንስ ም/ ፕሬዝዳንት ጋር ስላደረገችው ቆይታ ታስነብባለች። እንዲሁም በሩብ ዓመቱ የተከናወኑ ተግባራትን የሚያሳዩ ምስሎችን ተመልከቱልኝ ትላለች። ለመዝናኛ ያለቻቸውን ካርቱኖች እና ጽሑፎችም አካትታለች። ስለዚህም አንባብያን በዜና መጽሔቷ በኩል ያደረስንላችሁን ቁምነገሮች እየተዝናናችሁ እንድትገበዩ እጋብዛለሁ።*

*ወደፊት በዜና መጽሔቷ የመጀመሪያ ቅጽ የመጨረሻ ክፍል በባንካችን በ4ኛው ሩብ ዓመት የተከናወኑ ዐበይት ተግባራትን እና የባንካችንን የ2017 የበጀት ዓመት አፈጻጸም የተመለከቱ ጽሑፎች ይቀርባሉ። ሌሎችም ዜና መጽሔቷ በአንባብያን ጥቆማ እና አስተዋፅኦ ተመሥርታ የምታስነበብባቸው ጽሑፎች ይኖራሉ። ከዚህ አንጻር ደግሞ ዜና መጽሔቷን በጋራ ጥረት አሟልተን እና ፋይዳዋን አጉልተን እንድናስቀጥላት አደራ እላለሁ።*

*መልካም ንባብ!*

*አልሰን አሰፋ*
*የኮርፖሬት ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክተር*

# ዐበይት ክንውኖች

ማርታ ዘሪሁን

## ኢ.ን.ባ. የደንበኞች አገልግሎት ወርን በሰፋት እና በድምቀት አከበረ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የደንበኞች አገልግሎት ወር ብሎ የሰየመውን ሰፊ መርሐ ግብር ያካሄደው "የላቀ አገልግሎት፣ ደስተኛ ደንበኛ" በሚል መሪ ቃል ከታኅሣሥ 24 እስከ ጥር 25 ቀን 2017 ዓ.ም. ባሉት ቀናት በመላው የአገሪቱ ክፍሎች የተለያዩ ዝግጅቶችን በማከናወን ነበር።

መርሐ ግብሩ በመጀመሪያው ዕለት በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ቅጥር ግቢ በተከናወነ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ከተጀመረ በኋላ የመክፈቻ ሥነ ሥርዓቱ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር እና የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ አሕመድ ሽዴ፣ ሌሎች የመንግሥት የሥራ ሓላፊዎች እና የባንኩ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ የባንኩ ፕሬዝዳንት አቶ አቤ ሳኖ፣ ሌሎች የባንኩ የሥራ ሓላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም ከሁሉ በላይ የባንኩ ደንበኞች በተገኙበት ተካሂዷል፡፡

መርሐ ግብሩ ከባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በተጨማሪ በመላ ኢትዮጵያ በተሠራጩት የባንኩ የዲስትሪክት ጽ/ቤቶች እና ቅርንጫፎችም ነበር የተካሄደው።

የደንበኞች አገልግሎት ወር ከተከበረባቸው ዝግጅቶች መካከልም በዋናው መሥሪያ ቤት እስከ ጥር 3 ቀን 2017 ዓ.ም. ድረስ ተካሂዶ የባንኩን የዐሥርት ዓመታት ጉዞ እና አገልግሎቶች ያሳየ ዐውደ ርእይ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች፣ የደም ልገሳ ተግባራት እና ከደንበኞች ጋር የተደረጉ ውይይቶች ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።



የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ሲዘመር

ዐውደ ርእዩ በመርሐ ግብሩ የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ በተገኙ የክብር እንግዶች፣ በባንኩ የሥራ መሪዎች እና ሠራተኞች፣ በባንኩ ደንበኞች እና በተማሪዎች ተጎብኝቷል። የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎቹ እና ሌሎቹ ተግባራት ደግሞ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት እና በቅርንጫፎቹ ተካሂደዋል።

የባንኩ ፕሬዝዳንት አቶ አቤ ሳኖ በመርሐ ግብሩ መክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ "ደንበኞቻችን ስለምትተማመኑብን እጅግ እናመሰግናለን። ባንካችን ለደረሰበት ስኬት ላደረጋችሁት አስተዋፅኦ ሁሉ ክብር ይገባችኋል። ባንካችን እናንተን ለማገልገል ሁሌም ዝግጁ ሆኖ ይጠብቃችኋል። እንኳን ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የደንበኞች አገልግሎት ወር አደረሳችሁ!" ብለዋል።

ከደንበኞች ጋር ውይይት በተደረገባቸው አጋጣሚዎችም የባንኩ ከፍተኛ የሥራ መሪዎች ተመሳሳይ መልእክቶችን አስተላልፈዋል።

## ደንበኞችን ማእከል ያደረጉ በርካታ ውይይቶች ተካሄዱ

ኢ.ን.ባ. ከታኅሣሥ 24 እስከ ጥር 25 ቀን 2017 ዓ.ም. ባካሄደው የደንበኞች አገልግሎት ወር አከባበር መርሐ ግብር በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ደንበኞቹን ማእከል ያደረጉ ውይይቶችን አካሂደ።

ውይይቶቹ በተለይ በአዲስ አበባ፣ መቀሌ፣ ሻሸመኔ፣ ሐዋሳ፣ ድሬዳዋ፣ ሰመራ፣ ጅማ፣ አዳማ፣ ባሌ ጎባ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ሆሳዕና፣ ደብረ ማርቆስ፣ አምቦ፣ ደብረ ብርሃን፣ ሽሬ ዕንዳሥላሴ፣ ጎንደር እና አሰላ ከተሞች ከሚገኙ የባንኩ ደንበኞች ጋር ነበር የተካሄዱት።

ባንኩ በአዲስ አበባ እና በሐዋሳ ከተሞች ከወጪ ንግድ ደንበኞች፣ በቡታጅራ ከተማ ከሲቢኢ ኑር ደንበኞች፣ በሁሉም ከላይ የተጠቀሱ ከተሞች ደግሞ ከተለያዩ ደንበኞች ጋር ውይይት አድርጓል። ደንበኞቹ ከሆኑት በዋና መሥሪያ ቤቱ የተገኙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጋርም ተወያይቶ ነበር።

ውይይቶቹ በተካሄዱበት ወቅት የባንኩ የሥራ ሓላፊዎች ደንበኞች ከባንኩ ጋር አብረው በመሥራታቸው ምስጋና አቅርበው፣ ወደፊትም በለውጥ ሂደት ላይ ካለው ከባንኩ ጋር እንዲዘልቁ ጥሪ አቅርበዋል። በተጨማሪም የባንኩን አሠራር እና አገልግሎቶች የተመለከተ ግንዛቤ አስጨብጠዋል።

በውይይቶቹ የተሳተፉ ደንበኞች እና የከተማ ከንቲባዎችም ባንኩን የውይይት መድረክ በማዘጋጀቱ አመስግነው፣ አገልግሎቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል። የትግራይ ክልላዊ መንግሥት ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዝዳንት አቶ ጌታቸው ረዳ ደግሞ ባንኩ የተዳከመውን የትግራይ ክልል ኢኮኖሚ ለማነቃቃት የጀመራቸው ሥራዎች አበረታች እንደሆኑ ተናግረዋል።



*በሰመራ ከተማ ከሚገኙ ደንበኞች ጋር*

ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጋር በተደረገው ውይይት ወቅት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ብሩክ ታዬ የአገሪቱ ባንኮች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ተከትለው ስለሚሠሩ ባንኩ ዘርፉን የሚያነቃቃ ፈጠራ የታከለበት የፋይናንስ አገልግሎት መላ በመፍጠር የመሪነት ሚና ሊኖረው ይገባል ብለዋል።



*ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጋር*

በዚህ አጋጣሚም የባንኩ ፕሬዝዳንት አቶ አቤ ሳኖ ባንኩ በቅርቡ ደመወዛቸውን በባንኩ በኩል ለሚቀበሉ የመንግሥት የልማት ተቋማት ሠራተኞች በሲቢኢ ብር ፕላስ አገልግሎቱ አማካይነት አነስተኛ መጠን ያላቸውን ብድሮች ያለዋስትና የሚያቀርብበትን አሠራር ለመተግበር መዘጋጀቱን አሳውቀዋል፡፡

የባንኩ ደንበኞች ደግሞ የባንኩ አገልግሎት አሰጣጥ ጉልህ መሻሻል እያሳየ እንደሆነ ገልጸው ምስጋና ከማቅረብ ባሻገር፣ ባንኩ ወደፊት ሊያሻሽላቸው ይገባል ባሏቸው ጉዳዮች ላይ አስተያየት እና ጥያቄ ሰንዝረው፣ ከባንኩ የሥራ መሪዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ተቀብለዋል። በውይይት ክፍለ ጊዜዎች መጨረሻም የምስጋና የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል።

# የኢ.ን.ባ. የመንፈቀ ዓመት አፈጻጸም ተገመገመ

የኢ..ን.ባ. የ2017 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት አፈጻጸም ጥር 26 እና 27 ቀን 2017 ዓ.ም. በዋናው መሥሪያ ቤት በተካሄደ ከ1200 በላይ የሥራ አመራር አባላት የተሳተፉበት ጉባኤ ተገምግሟል።

በጉባኤው ላይ ባንኩ በመንፈቅ ዓመቱ 245.9 ቢሊዮን ብር ተቀማጭ ገንዘብ አሰባስቦ የተቀማጭ የገንዘብ መጠኑን ከ1.4 ትሪሊዮን ብር በላይ እንዳደረሰ እና በተመሳሳይ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተሰበሰበው ጠቅላላ ተቀማጭ ገንዘብ 58.3 በመቶ ድርሻ እንደያዘ ተገልጿል።

በተጨማሪም ባንኩ በመንፈቅ ዓመቱ 153.32 ቢሊዮን ብር ብድር (88 በመቶ ያህሉን ለግሉ ዘርፍ) ሰጥቶ አጠቃላይ የብድር ክምችቱን ከ1.3 ትሪሊዮን ብር በላይ እንዳደረሰ እና የብድር አገልግሎቱን በእያንዳንዱ ቤት ለማስገባት እየሠራ እንደሆነ ተነግሯል።

እንዲሁም በስድስቱ ወራት ከ910 ሚሊዮን በሚልቁ ግብይቶች ከ5.4 ትሪሊዮን ብር በላይ የገንዘብ እንቅስቃሴ በባንኩ ዲጂታል የክፍያ አማራጮች አማካይነት ተከናውኖ፣ በእነዚህ አማራጮች የሚከናወኑ ግብይቶች ከአጠቃላይ በባንኩ የተሳለጡ ግብይቶች ወደ 80 በመቶ የሚጠጋውን ድርሻ እንደያዙ ታውቋል፡፡

ግምገማው በቀጣናዎች፣ በዲስትሪክት ጽ/ቤቶች እና በቅርንጫፎች አፈጻጸም እንዲሁም በሌሎች የባንክ አገልግሎት ጉዳዮች ላይ ጭምር ተካሂዷል።

በመጨረሻም ጉባኤው የተቀማጭ ገንዘብ እና የውጭ ምንዛሪ ግኝት መጠንን ማሳደግን፣ በዲጂታል የባንክ አገልግሎት በመሪነት መቀጠልን፣ የብድር አቅርቦት ተደራሽነትን ማስፋትን እንዲሁም የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻልን እና ከተለያዩ ደንበኞች ጋር ያለን ግንኙነት ማጠናከርን ያካተቱ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ተጠናቅቋል።

የባንኩ አፈጻጸም የካቲት 19 ቀን 2017 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሓላፊዎች ጋር በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በተካሄደ ስብሰባ ላይም ተገምግሞ ነበር። በዚያም ባንኩ የተበላሸ ብድሩን መጠን በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱ፣ የሲቢኢ ኑር ወለድ አልባ አገልግሎቱን ማስፋፋቱ እና የ5 ዓመት ስልታዊ ዕቅድ እያዘጋጀ መሆኑ በተጨማሪ ጠንካራ ጎንነት ተነሥተዋል።

በዚያ ወቅት የገምጋሚ ተቋሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ብሩክ ታዬ ባንኩ የተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰቡን አጠናክሮ የገበያ ድርሻውን ይበልጥ ከፍ እንዲያደርግ፣ የብድር አሰጣጡን ሂደት ዲጂታላይዝ በማድረግ እና ተደራሽነቱን በማስፋት የደንበኞችን እርካታ ይበልጥ እንዲያሳድግ፣ ከሀገር ውጭ ያለውን ተደራሽነት እንዲያሰፋ እና የውጭ ባንኮች ወደ ሀገር በሚገቡበት ወቅት የሚያጋጥመውን ውድድር ተቋቁሞ የገበያ

ድርሻውን የሚያስጠብቅበትን ስትራቴጂ ከወዲሁ እንዲነድፍ አሳስበዋል።



*በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሲገመገም*

## ለሥራ ፈጠራ ውድድር አሸናፊዎች የብድር ቃል ተገባ

የብድር ቃል የተገባላቸው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር ባዘጋጀው ነጋድራስ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሥራ ፈጠራ ውድድር 3ኛ ምዕራፍ ለፍጻሜ የደረሱ 5 ተወዳዳሪዎች ነበሩ።

የካቲት 30 ቀን 2017 ዓ.ም. በኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በተካሄደው የፍጻሜ ውድድር አብርሃም እና አብዲ የተባሉ ተወዳዳሪዎች የኤሌክትሪክ ሞተር ብስክሌት የፈጠራ ሥራ በማቅረብ የ1 ሚሊዮን ብር ሽልማቱን ወስደዋል።

ሙሉዓለም እና ምስጋናው፣ አበባው እና አማረ፣ ዶ/ር ደሳለው እና አምሳሉ የተባሉ ተወዳዳሪዎች ደግሞ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያለውን ደረጃ አግኝተዋል።



ቃል የተገባው በ30 ተወዳዳሪዎች ተጀምሮ 4 ወራትን ለፈጀው ውድድር 5 የመጨረሻ አሸናፊዎች ለእያንዳንዳቸው 10 ሚሊዮን ብር ያለማስያዣ ለማበደር ነበር።

## ለ2 የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፎች ተደረጉ

የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው መቄዶንያ የአረጋውያን እና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማእከል እና ባቡል ኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅት ነበሩ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የካቲት 30 ቀን 2017 ዓ.ም.፣ ባንኩ የሚያስተዳድረው ኮሜርሻል ኖሚኒስ ሓላ/የተ/የግ/ ማኅበር ደግሞ ሁለት ቀናት ቀድሞ ለማእከሉ ድጋፍ በሚሰባሰብበት ስቱዲዮ በመገኘት በአጠቃላይ የ33 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማረጋገጫ ሰጥተዋል።

ባንኩ ያበረከተው በሠራተኞቹ እና በባንኩ የተዋጣ የ30 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ሲሆን፣ ማኅበሩ ያበረከተው 2 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ ፍጣዎች፣ በሠራተኞቹ እና በራሱ የተዋጣ አጠቃላይ 500 ሺሕ ብር እንዲሁም 500 ሺሕ ብር የሚገመት የፅዳት አገልግሎት ነው።

የመቄዶንያ መሥራች እና የበላይ ጠበቂ የክብር ዶክተር ብንያም በለጠ በበኩላቸው ባንኩ እና ማኅበሩ በተደጋጋሚ ለማእከሉ ላደረጉት ድጋፍ ምስጋና አቅርበው፣ በቀጣይም ከጎኑ እንዲቆሙ ጠይቀዋል።




ባንኩ ከ4,800 በላይ አባወራዎችን ለሚመግበው ባቡል ኸይር መጋቢት 3 ቀን 2017 ዓ.ም. የረመዷን ወርን ምክንያት በማድረግ ነበር በማእከሉ ተገኝቶ ለተቸገሩ ወገኖች የሚውል የ15 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ያደረገለት።

## ኢ.ን.ባ. ዓለም አቀፍ የካርድ አገልግሎቶችን አቀረበ

ባንኩ ያቀረበው የፕላስቲክ እና የቨርቹዋል ካርድ አገልግሎቶችን ሲሆን፣ ከማስተርካርድ ኩባንያ ጋር በመተባበር መጋቢት 18 ቀን 2017 ዓ.ም. በዋና መሥሪያ ቤቱ በተከናወነ ሥነ ሥርዓት ሥራ አስጀምሯቸዋል።

በሥነ ሥርዓቱ ላይ የባንኩ ፕሬዝዳንት አቶ አቤ ሳኖ ባንኩ ከማስተርካርድ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት የታተመ የክፍያ ካርድ አገልግሎት እና ከሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ጋር የተጣመረ ቨርቹዋል የክፍያ ካርድ አገልግሎት እንደሚሰጥ አሳውቀዋል፡፡

አክለውም አገልግሎቶቹ ዘመናዊ፣ ፈጣን፣ ደኅንነታቸው የተጠበቀ፣ የክፍያ ሥርዓቱን አንድ ደረጃ ከፍ በማድረግ ዓለም ዓቀፍ አገልግሎት ማግኘት የሚያስችሉ እና ግዥን የሚያቀላጥፉ እንደሆኑ ገልጸዋል።




*ዓለም አቀፍ ካርዶችን ሥራ ለማስጀመር*

የባንኩ ደንበኞች የፕላስቲክ ክፍያ ካርዱን ከባንኩ ቅርንጫፎች፣ የቨርቹዋል ካርድ አገልግሎቱን ደግሞ ከባንኩ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት መተግበሪያ ማግኘት እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡

የማስተርካርድ በአፍሪካ ፕሬዝዳንት ማርክ ኢሊየት በበኩላቸው አገልግሎቶቹ የባንኩን የዲጂታል ስትራቴጂ በማሳካት ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ውስጥ ያላትን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እንደሚያግዙ ተናግረዋል፡፡ ኩባንያቸው በምሥራቅ አፍሪካ ቀዳሚ ከሆነው ኢ.ን.ባ ጋር ስትራቴጂያዊ አጋርነት በመፈጸሙ ኩራት እንደሚሰማውም ገልጸዋል፡፡

## የሶደቃ እና የኢፍጣር መርሐ ግብሮች ተካሄዱ

ኢ.ን.ባ. የ1446ኛው ዓ.ሒ. የረመዷን ወርን ምክንያት በማድረግ "አብሮነት ለበጎነት በረመዷን" በሚል መሪ ቃል በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በተለያዩ ቀናት የማዕድ ማጋራት እና የኢፍጣር መርሐ ግብሮችን አካሄደ።

የማዕድ ማጋራት መርሐ ግብሩ የተካሄደው በደሴ፣ ሻሸመኔ፣ ሰመራ፣ ጅማ፣ ድሬዳዋ፣ ጂግጂጋ፣ ባሌ ሮቤ፣ አሶሳ፣ ቁሮ፣ አሰላ፣ መቱ እና መቀሌ ከተሞች ለሚገኙ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች የነበረ ሲሆን፣ የኢፍጣር መርሐ ግብሩ የተከናወነው ደግሞ በተለይ በሻሸመኔ፣ አዲስ አበባ፣ መቱ እና ጂግጂጋ ከተሞች ለሚኖሩ የባንኩ ደንበኞች ነበር።



*በመቱ ከተማ የተካሄደ ኢፍጣር*

በሶደቃ እና ኢፍጣር መርሐ ግብሮቹ ላይ የባንኩ የሥራ ሓላፊዎች ባንኩ መርሐ ግብሮቹን ያካሄደው ከሙስሊሙ ኅብረተሰብ ጋር ያለውን አብሮነት ለማሳየት እንደሆነ ገልጸዋል።

የሶደቃ ተጠቃሚዎችም የምግብ ግብአቶች ሰስለተሰጧቸው ደስታ እንደተሰማቸው ተነናግረው፣ ለባንኩ ምስጋና አቅርበዋል።

በሶደቃ እና ኢፍጣር መርሐ ግብሮች የተገኙ የክብር እንግዶች በበኩላቸው ባንኩን በየአካባቢያቸው ላደረጋቸው አስተዋፅኦዎች አመስግነው፣ የሰብአዊነት ተግባራቱን እና የሲቢኢ ኑር አገልግሎቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል።

## የፖስ ማሽን ተጠቃሚዎች ተሸለሙ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የገና እና የጥምቀት በዓላትን እንዲሁም የረመዷን ወርን ምክንያት በማድረግ ለፖስ ማሽን አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ባዘጋጀው የሽልማት መርሐ ግብሮች የዕጣ አሸናፊ የሆኑ ባለዕድሎችን በየጊዜው ለይቶ በማሳወቅ ሽልማት አበርክቷል።

መርሐ ግብሮቹ ከታኅሣሥ 21 እስከ የካቲት 16 ቀን 2017 ዓ.ም. ድረስ ከብር 1,000 ጀምሮ በፖስ ማሽን ተገበያይተው የገና እና የጥምቀት በዓል ዕጣዎችን ያሸነፉ 315 ደንበኞችን እና ከየካቲት 28 እስከ መጋቢት 22 ቀን ተመሳሳይ ግብይት ፈጽመው የረመዷን ወር ዕጣዎችን ያሸነፉ 100 ደንበኞችን የ10 ሺ. ብር ሽልማት ባለዕድል የሚያደርጉ ነበሩ።

እነዚህ መርሐ ግብሮች ደንበኞች ዲጂታል የባንክ

አገልግሎቶችን እንዲጠቀሙ ለማበረታታት እንደተዘጋጁ ተገልጿል፡፡



## ኢ.ን.ባ. ከ2 ተቋማት ጋር ስምምነቶችን ተፈራረመ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2017 የበጀት ዓመት 3ኛው ሩብ ዓመት ከየሁሉ የብድር እና ቁጠባ የኅብረት ሥራ ማኅበር እና ከሻሻመኔ ከተማ አስተዳደር ጋር አብሮ ለመሥራት ስምምነቶችን ተፈራርሞ ነበር።

በባንኩ የዲጂታል ባንኪንግ ም/ፕሬዝዳንት  አቶ ወጋየው ገ/ማርያም  እና በኅብረት ሥራ ማኅበሩ የቦርድ ሊቀመንበር አቶ መሳፍንት ደበበ የተፈረመው ስምምነት ዝቅተኛ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ የተሰማሩ የማኅበሩ ደንበኞችን ገንዘብ ለመቆጠብ፣ ለማስተላለፍ እና ለመበደር የሚያስችል የሥራ አጋርነት እንደፈጠረ ተነግሯል፡፡

በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ደንበኞች ቁጥር ከ20 ሺሕ ወደ 100 ሺሕ ለማሳደግ፣ የማኅበሩን ቅርንጫፎች ለማስፋፋት እና የፋይናንስ አካታችነትን እውን ለማድረግ እንደሚያግዝ ተገልጿል።

በሌላም በኩል በኢ.ን.ባ. የሻሸመኔ ዲስትሪክት ዳይሬክተር አቶ ደዋኖ ሑሴን እና  በከተማ አስተዳደሩ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ደምሴ ንዮሬ የተፈረመው ስምምነት በሻሻመኔ ከተማ የሚገኙ ደንበኞች ወርኃዊ የውሀ ፍጆታ ክፍያቸውን በሲቢኢ ብር አገልግሎት እንዲፈጽሙ ያስችላል ተብሏል።



## ረጅም ጊዜ ላገለገሉ ሠራተኞች ሽልማት እና ዕውቅና ተሰጠ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዋና መሥሪያ ቤቱ በተከናወነ ሥነ ሥርዓት ባንኩን ለ25 እና 15 ዓመታት ላገለገሉ 392 የዋናው መሥሪያ ቤት ሠራተኞች የወርቅ የደረት ፒን ሽልማት እና የዕውቅና የምስክር ወረቀት አበርክቷል፡፡

በዚህም የባንኩ ፕሬዝዳንት አቶ አቤ ሳኖ የ15 ዓመታት፣ የባንኩ የሰው ኃይል አስተዳደር ም/ ፕሬዝዳንት አቶ ኤፍሬም መኩሪያ ደግሞ የ25 ዓመታት አገልግሎት ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

አቶ አቤ የባንኩ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያን ማገልገል እንደሆነ እና በርካታ ባንኩ ያሠለጠናቸው ሠራተኞች በተለያዩ ባንኮች በመሥራት ላይ እንደሚገኙ እንዲሁም አዲሱ ትውልድ ተቋም የመገንባት እና የመጠበቅ ክህሎትን ረጅም ልምድ ካላቸው ሠራተኞች ሊወስድ  እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡



የባንኩ የሰው ኃይል ም/ ፕሬዝዳንት አቶ ኤፍሬም መኩሪያ በበኩላቸው ባንኩ በጥቂት ሠራተኞች ሥራ ጀምሮ በትውልድ ቅብብል ስኬታማ ጉዞ እንዳደረገ እና በዚህ ወቅት ከ80 ሺህ በላይ ቋሚ እና ጊዜያዊ ሠራተኞች እንዳሉት አሳውቀዋል።

## የደንበኞች ግንኙነት ማእከል አገልግሎት ማሻሻያ ፕሮጀክት ተተገበረ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የደንበኞች ግንኙነት ማእከሉን አገልግሎት ለማሻሻል የቀረፀው ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አቶ ዐቢይ ጌታቸው ባንኩ በ951፣ በ847 እና በ915 አጭር የጥሪ መሥመሮች ደንበኞቹን የሚያስተናግድበት አቫያ የተሰኘ አዲስ እና የዘመነ ሥርዓት በጥሪ ማእከሉ ላይ ተግባራዊ እንዳደረገ አስታውቀዋል።

አክለውም ማሻሻያው የሲቢኢ ብር ደንበኞች በ847 አጭር የጥሪ መሥመር በመደወል፣ በፖስ ማሽን የሚያገበያዩ ድርጅቶች ደግሞ በ915 አጭር የጥሪ መሥመር በመደወል እንዲስተናገዱ እንዳደረገ ገልጸዋል።

በተጨማሪም ፕሮጀክቱ በባንኩ ድረ ገጽ፣ የማኅበራዊ ትስስር ገጾች እንዲሁም የሞባይል ባንኪንግ እና የሲቢኢ ብር መተግበሪያዎች ላይ በቅርቡ ሥራ በሚጀምር ቻትቦት አማካይነት የደንበኞችን ጥያቄ ማስተናገድ እንደሚያስችል ተናግረዋል።

ማሻሻያው ደንበኞች የባንኩን አገልግሎቶች በራስ አገዝ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ስለሚያስችል የጥሪ ማእከሉን ጫና እንደሚቀንስ ተጠቁሟል።



# ከ4 የክልል መንግሥታት ጋር ውይይቶች ተካሄዱ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሲዳማ፣ ከማእከላዊ ኢትዮጵያ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ እና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ጋር አብሮ ለመሥራት ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ውይይቶችን አካሂዷል።

የባንኩ የሥራ አመራር አባላት ከሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርእሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ጋር ባረጉት ውይይት ላይ የባንኩ የሪቴል እና ቅርንጫፍ ባንኪንግ ዋና ም/ ፕሬዝዳንት አቶ ደረጀ ፉፋ ባንኩ በክልሉ ያሉ የኢንቨስትመት እንቅስቃሴዎችን እና በግሉ ዘርፍ የሚታየውን የኢኮኖሚ መነቃቃት ለማገዝ ቁርጠኛ እንደሆነ ተናግረዋል። ርእሰ መስተዳድሩ በበኩላቸው ባንኩ በክልሉ ለሚያደርገው ሰፊ እንቅስቃሴ እና ግንኙነት ምስጋና አቅርበው፣ ቁርጠኝነቱን የገለጸበትን እገዛ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል። ክልሉ ከባንኩ ጋር አብሮ እንደሚሠራም አረጋግጠዋል።



*ከሲዳማ ክልል መንግሥት ጋር*

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የደቡብ ምዕራብ ሪጅን ም/ ፕሬዚዳንት አቶ ሙሉነህ ለማ እና የሆሳዕና ዲስትሪክት አመራሮች ከማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ርእሰ መስተዳድር ዶ/ር እንዳሻዉ ጣሰው ጋር ባደረጉት ውይይት ላይ ደግሞ ባንኩ የክልሉን የልማት ሥራዎች ይበልጥ መደገፍ በሚችልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ምክክር ተደርጓል። በምክክሩ ሂደት ዶ/ር እንዳሻው ባንኩ የኑሮ ዉድነትን ለማረጋጋት፣ ለመኖሪያ ቤት ልማት እንዲሁም ምርት እና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ ግብአቶችን በሚያመቻቹ መስኮች ለተሰማሩ ባለሀብቶች እና የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያደርገውን ድጋፍ እንዲያጠናክር አሳስበዋል። አቶ ሙሉነህ በበኩላቸው ባንኩ ከክልሉ መንግሥት ጋር ተቀራርቦ የኢኮኖሚ ግንባታዉን ሂደት ለመደገፍ እና የደንበኞችን ፍላጎት ለማሟላት በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል።



*ከማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ጋር*

የኢ.ን.ባ. የሪቴል እና ቅርንጫፍ  የባንክ አገልግሎት ዋና ም/ ፕሬዝዳንት አቶ ደረጀ ፉፋ፣  የባንኩ የደቡብ ምእራብ ቀጣና ም/ ፕሬዚዳንት አቶ ሙሉነህ ለማ እና የወላይታ ሶዶ ዲስትሪክት የሥራ ሓላፊዎች ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርእሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ ጋር ባደረጉት ውይይት ላይ ደግሞ ባንኩ የክልሉን የልማት ሥራዎች ይበልጥ መደገፍ በሚችልባቸዉ ጉዳዮች ዙሪያ ተመካክረዋል። በምክክሩም ወቅት አቶ ጥላሁን ከበደ ባንኩ በቱሪዝም፣ በግብርና፣ በብድር አቅርቦት እና በባንክ አገልግሎት ተደራሽነት ዙሪያ የሚሰጠውን አገልግሎት አጠናክሮ እንዲቀጥል የጠየቁ ሲሆን፣ የኢ.ን.ባ. ልኡካን ቡድን ባንኩ ለጥያቄያቸው ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት እንደሚሠራ አረጋግጧል።

በኢ.ን.ባ. የደቡብ ምዕራብ ቀጣና ም/ ፕሬዝዳንት አቶ ሙሉነህ  ለማ የተመራ የልኡካን ቡድን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርእሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን ጋር ባንኩ በክልሉ ወረዳዎች ተደራሽነቱን ማስፋት በሚችልባቸው እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተወያይቷል። በውይይቱ ወቅት አቶ አሻድሊ በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ አመኔታን ያተረፈው ኢ.ን.ባ. በክልሉ ወረዳዎች ላይ ያለውን ውስን ተደራሽነት እንዲያሰፋ እንዲሁም የክልሉን ኅብረተሰብ የብድር አቅርቦት

ተጠቃሚነትን ለማሳደግ እንዲቻል ባንኩ በአሶሳ ከተማ የዲስትሪክት ጽ/ቤት እንዲከፍት ጠይቀዋል።

የባንኩ ልኡካንም ባንኩ ተደራሽነቱን ለማስፋት በቅርቡ በሸርቆሌ እና ኩርሙክ ወረዳዎች ቅርጫፎችን ለመክፈት እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ፣ በቀጣይ በሌሎችም ወረዳዎች ተደራሽ ለመሆን እንደሚሠራ እና የብድር አቅርቦቱን ተደራሽ ለማድረግ ከቀጣይ ዓመት ጀምሮ ቅርንጫፎቹ ዐቅማቸው አድጎ ሰነዶችን በማደራጀት የብድር አቅርቦት ሥራዎችን እንዲያሳልጡ ለማድረግ  አቅጣጫ ተይዞ እንደሚሠራ ተናግረዋል።



*ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ጋር*



*ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት ጋር*

# የሲቢኢ ኑር አገልግሎት 5 ሽልማቶችን ተቀዳጀ

አልማቲን ኮንሰልተንሲ ሰርቪስ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት እና ከሳዲያ መልቲሚዲያ ጋር በመተባበር አዲስ አበባ በሚገኘው ስካይላይት ሆቴል ባካሄደው የመጀመሪያው ከወለድ ነጻ የፋይናንስ ጉባኤ እና የሽልማት መርሐ ግብር ላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ለውድድር ከቀረቡ 9 ዘርፎች በአምስቱ አሸናፊ ሆኗል፡፡

ከሽልማቶቹ አንዱ የባንኩ ፕሬዝዳንት አቶ አቤ ሳኖ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት በኢትዮጵያ እንዲጀመር እና አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የተሰጠ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ ለሲቢኢ ኑር ም/ ፕሬዚዳንት አቶ ኑሪ ሑሴን በወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት የላቀ ባለሙያ መሆናቸውን ለመመስከር የቀረበ  ሽልማት ነበር፡፡

ቀሪዎቹ ሽልማቶች ደግሞ ኢ.ን.ባ. በኢንዱስትሪው ከ70 በመቶ በላይ የሚሆነውን የሰው ኃይል ድርሻ በመያዙ፣ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎትን በኢትዮጵያ በማስጀመሩ እና በዓመቱ የላቀ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት በመስጠቱ ያገኛቸው እንደሆኑ ተገልጿል፡፡




# የሠራተኞች ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማኅበር ምሥረታ ጉባኤ ተካሄደ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሠራተኞች ሓላፊነቱ የተወሰነ ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማኅበር ምሥረታ ጉባኤ መጋቢት 28 ቀን 2017 ዓ.ም. በባንኩ የዛግዌ ሕንጻ መሰበሰቢያ አዳራሽ ተካሂዷል፡፡

በጉባኤው ላይ የባንኩ ፕሬዝዳንት አቶ አቤ ሳኖ በተወካያቸው አቶ ነቢዩ ሰለሞን በኩል “ማኅበሩ በቀጣይ በሚያከናውናቸው ተግባራት የባንካችንን ሠራተኞች ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ጠንክሮ ሊሠራ ይገባዋል፡፡ ትልቅና አትራፊ ማኅበር በመሆንም የተነሣበትን ዓላማ አሳክቶ የባንካችንን ስም በመልካም ሥራ እንደሚያስጠራ አልጠራጠርም፡፡“ ብለዋል፡፡

ጉባኤው የኅብረት ሥራ ማኅበሩን 9 የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት እና 3 የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ምርጫ አከናውኗል፡፡



*ተመራጮች ቃለ መሐላ ሲፈጽሙ*

# ባንካችን የአውሮፓ ፊልም ፌስቲቫልን በአጋርነት አዘጋጀ

በየዓመቱ በአውሮፓ ኅብረት የሚዘጋጀው እና ዘንድሮ እ.ኤ.አ. ከጥር 31 እስከ መጋቢት 9 ቀን 2025 ድረስ የተከናወነው የአውሮፓ ፊልም ፌስቲቫል የመክፈቻ መርሐ ግብር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋናው መሥሪያ ቤት የጉባኤ አዳራሽ ተከናውኗል፡፡

በመክፈቻ መርሐ ግብሩ ላይ የባንኩ የሥራ አመራር እንዲሁም በአውሮፓ ኅብረት በኩል ጥሪ የተደረገላቸው ዲፕሎማቶች፣ አምባሳደሮች እና ሌሎች እንግዶች የተገኙ ሲሆን፣ ዛቶፔክ / Zátopek/ የተሰኘ የቼክ ሪፐብሊክ ፊልም ለዕይታ ቀርቧል።

ፌስቲቫሉ 28 ከአውሮፓ እና 2 ከኢትዮጵያ የተመረጡ ፊልሞች ለዕይታ በመቅረባቸው ከእነሱ ብዛት እንዲሁም የኢትዮጵያ እና የአውሮፓ ኅብረት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የመሠረቱበት 50ኛ ዓመት በሚከበርበት ወቅት ከመካሄዱ አንጻር በዓይነቱ የተለየ እንደሆነ ተገልጿል።




# መዝናኛ

## ይበዛብኛል!

አንድ በሙከራ ቅጥር ላይ ያለ አዲስ የባንክ ሠራተኛ የተሰጠውን ሒሳብ የማስከፈት ሥራ በፍጥነት እና በከፍተኛ ደረጃ በማከናወኑ አለቃው በብቃቱ ተደንቀው ብዙ ተቀማጭ ገንዘብ እንዲያሰባስብ ይመድቡታል። ሠራተኛው ግን ቅር በመሰኘት ይህ ሥራ እንደሚከብደው ይነግራቸዋል። ምክንያቱን ሲጠይቁት እያቅማማ “ሒሳቦቹን ያስከፈትሁት በራሴ ገንዘብ ነበረ። እርሶ ያሉትን ያህል ተቀማጭ ለማሰባሰብ እኮ የ10 ዓመት ደሞዜን ማስቀመጥ አለብኝ ማለት ነው!” አላቸው።




"That's our rate for overnight loans."

ምንጭ፡- https://www.cartoonstock.com/cartoon?searchID=CS296743

# ስኬታችን

አስቻለዉ ተክሉ

## የደረስንበት

## እስከ 2017 የበጀት ዓመት 3ኛ ሩብ ዓመት መጨረሻ

### የአገልግሎቶቻችን ተጠቃሚዎች

42.1 ሚሊዮን ሒሳብ የከፈቱ ደንበኞች

31.2 ሚሊዮን የሲቢኢ ብር አገልግሎት ተጠቃሚዎች

16.0 ሚሊዮን የካርድ ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚዎች

10.0 ሚሊዮን የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚዎች

40.6 ሺሕ የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚዎች

### አገልግሎቶቻችንን ያሳለጡ

80,061 ቋሚ እና ጊዜያዊ ሠራተኞች

1,924 (155 ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነጻ) ቅርንጫፎች እና 60 ንኡሳን ቅርንጫፎች

4,012 ኤቲኤሞች

6,282 የፖስ ማሽኖች

73,547 ወኪሎች

141,324 አጋር ነጋዴዎች

### በአገልግሎቶቻችን ያሳካናቸው

1.563 ትሪሊዮን ብር አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ (48.8% የገበያ ድርሻ) ማሰባሰብ

2.66 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘት እና 5.81 ቢሊዮን ዶላር መክፈል

2.107 ትሪሊዮን ብር አጠቃላይ ሀብት (50.0% የገበያ ድርሻ) መያዝ (የየካቲት 28፣ 2025 እ.ኤ.አ. መረጃ)

የ134.1 ቢሊዮን ብር አጠቃላይ ካፒታል (31.5% የገበያ ድርሻ) ባለቤት መሆን (የጥር 31፣ 2025 መረጃ)

የሰጠነውን አጠቃላይ ብድር 1.435 ትሪሊዮን ብር (50.3% የገበያ ድርሻ) ማድረስ

የተበላሸብንን ብድር መጠን ወደ 2.1% ዝቅ ማድረግ

ካስተናገድናቸው አጠቃላይ ግብይቶች 79.2% ያህሉን በዲጂታል ቻናሎች ማሳለጥ

የተቋማዊ ለውጥ እና ማሻሻያ ውጥኖች ትግበራችንን 95.6% ማድረስ

*ምንጭ፦ የኢ.ን.ባ. የ2017 የበጀት ዓመት 9 ወራት የአፈጻጸም ሪፖርት*

# የባንክ አገልግሎት

## የላቀ አገልግሎት፣ ደስተኛ ደንበኛ!

ተመስገን ጻምጠዉ

***ዐውደ ንዋይ*** *በ3ኛው ሩብ ዓመት የተከበረውን የኢ.ን.ባ. የደንበኞች አገልግሎት ወር በተመለከተ ከባንካችን የካስተመር ኤክስፒሪየንስ ም/ፕሬዝዳንት አቶ ኃይለየሱስ በቀለ ጋር ቆይታ አድርጋ ነበር። ከእሳቸው ጋር የነበረንን ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።*




<u>ዐውደ ንዋይ፡-</u> የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከታኅሣሥ 24 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ የደንበኞች አገልግሎት ወርን "የላቀ አገልግሎት ደስተኛ ደንበኛ" በሚል መሪ ቃል ማክበሩ ይታወቃል፡፡ የአከባበሩ መነሻና ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ምንድን ነበር?

<u>አቶ ኃይለየሱስ፡-</u> ከመነሻው ልጀምር። ባለፉት አምስት ዓመታት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዘመናዊ አሠራሮችን ለመዘርጋትና ዘላቂነት ያለው እድገትን ለማሰቀጠል በሚያስችሉ ተግባራት ላይ ትኩረት ያደረገ የለውጥና ትራንስፎርሜሽን ትግበራ ማከናወኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ የትራንስፎርሜሽን ሂደት ውስጥ ከተከናወኑ ስኬታማ እርምጃዎች መካከል አገልግሎትን/ምርትን መሠረት ካደረገ የቢዝነስ ሞዴል ወደ ደንበኛ ተኮር የአሠራር ሥርዓት መሸጋገር ዋናው ነው፡፡ የቅርንጫፍ አሠራር ሂደትና አደረጃጀትም ይህንኑ ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ ከዚህ አኳያ 2017 ዓ.ም. ባንካችን ወደ ደንበኛ ተኮር የአሠራር ሥርዓት ሽግግር አድርጎ አመርቂ ውጤት እያስመዘገበ ያለበት ወቅት በመሆኑ የደንበኞች አገልግሎት ወር አከባበር ይህን እንዲያንጸባርቅ ማድረግ ያስፈልግ ነበር፡፡

በዚህ ምክንያት ባንካችን የደንበኞች አገልግሎት ወርን ካለፉት ዓመታት በተለየ መልኩ በዚህ ዓመት "የላቀ አገልግሎት ደስተኛ ደንበኛ" በሚል መሪ ቃል አክብሯል፡፡ ወሩን ማክበር ያስፈለገው በዋናነት፡-

- የባንካችን ዘለቄታዊ ስኬት በደንበኞቻችን እርካታና ዘላቂ ግንኙነት ላይ ለመመሥረቱ ዕውቅና ለመስጠትና ለስኬታችን መሠረት ለሆኑት ደንበኞቻችን ምስጋና ለማቅረብ፣
- ከደንበኞቻችን ጋር ፊት ለፊት የምንወያይበትን መድረክ በመፍጠር ከእነሱ ገንቢ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ግብአቶችን ለማግኘት፣
- ከደንበኞቻችን ጋር ያለንን የሥራ ግንኙነት ለማጠናከርና ፍላጐታቸውን መሠረት ያደረገ አገልግሎት ለመስጠት ያለንን ዝግጁነት ለማሳየት፣
- ባንካችን በሀገሪቱ የፋይናንስ ኢንዱስትሪ መሪ እንደመሆኑ መጠን፣ ለአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል ያለውን ቁርጠኝነት ለማሳየት፣
- እንዲሁም ባንካችን ለሌሎች ፋይናንስ ተቋማት ተሞክሮዎችን እንዲያካፍል እና አርዓያ እንዲሆን ለማድረግ ነበር፡፡

<u>ዐውደ ንዋይ፡-</u> የ2017 ዓ.ም. የደንበኞች አገልግሎት ወር በተለያዩ ዝግጅቶች መከበሩ ይታወቃል፡፡ ዝግጅቶቹንና ፋይዳዎቻቸውን ቢገልጹልን?

<u>አቶ ኃይለየሱስ፡-</u> በ2017 ዓ.ም የደንበኞች አገልግሎት ወር አከባበር መርሐ ግብር የተካተቱ ዋና ዋና ዝግጅቶች፡--

- ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማት የተጋበዙ ከፍተኛ የሥራ ሓላፊዎችን እንዲሁም የባንኩን የሥራ አመራር ቦርድና የሥራ አመራር አባላት፣ ሠራተኞችና ደንበኞች በሰፊው ያካተተ የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት፣
- ባንካችን ከምሥረታው ጀምሮ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ ምን ይመስል እንደነበርና አሁን ላይ በምን ደረጃ ላይ

እንደሚገኝ ለማሳየት የባንኩን የስምንት ዐሠርት ዓመታት የአገልግሎት አሰጣጥ ጉዞ ያስቃኘ ዐውደ ርእይ፣

- ከተለያዩ ደንበኞች ማለትም፡- ከሪቴይል፣ ከብድር፣ ከዓለማቀፍ የባንክ አገልግሎት፣ ከወለድ አልባ የባንክ አገልግሎት፣ ከመንግሥት የልማት ድርጅቶችና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ደንበኞች ጋር በዋናው መሥሪያ ቤትና በሁሉም የባንኩ የዲስትሪክት ጽ/ቤቶች የተካሄዱ የፊት ለፊት የመድረክ ውይይቶች፣
- የደንበኞች ወርን በማስመልከት በሁሉም የሥራ ክፍሎች የተካሄዱ የደንበኞች አገልግሎትን የሚመለከቱ የጠዋት ክፍለ ጊዜ ውይይቶች፣
- የባንኩን የመልእክት ማስተላለፊያ አውታሮች በመጠቀም በባንካችን ፕሬዝዳንት አማካይነት ለባንካችን ደንበኞች የተላለፈ የምስጋና መልእክት፣ እና
- መርሐ ግብሩን ምክንያት በማድረግ የተከናወኑ የደም ልገሳ እና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡



*ዐውደ ርእይ የጎበኙ ተማሪዎች*





*በአዳማ ከተማ በተደረገ ዉይይት ላይ*

የዝግጅቶቹን ፋይዳዎች ስንመለከት፣ አንዱ ደንበኞቻችን ባንኩ ስላከናወናቸው የለውጥ ሥራዎችና ለውጡ ስላስገኘቸው ትሩፋቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ትልቅ ሥራ መሠራቱ ነው፡፡ ሁለተኛው የውይይት መድረኮች ደንበኞች በባንኩ አሠራር ላይ የነበሯቸውን ቅሬታዎችም ሆነ ጥያቄዎች እንዲያነሡ ዕድል በመፍጠራቸው፣ ደንበኞች ላቀረቧቸው ጥያቄዎች ከሚመለከታቸው የባንኩ ሓላፊዎች ምላሽ እንዲያገኙ መደረጉ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በደንበኞች የተነሡት ቅሬታዎች ባንኩ ከአገልግሎት አሰጣጥ አኳያ ያለበትን ክፍተት ተረድቶ ጠቃሚ የማሻሻያ ግብአቶችን እንዲያገኝ ማስቻላቸው ነበር።

**ዐውደ ንዋይ፡- የደንበኞች አገልግሎት ወር የተከበረባቸው ዝግጅቶች ምን ያህል ዓላማዎቻቸውን እንዳሳኩ ቢያስረዱን?**

አቶ ኃይለየሱስ፡- የ2017 ዓ.ም. የደንበኞች አገልግሎት ወር አከባበር መርሐ ግብር የባንኩን የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣ የሥራ አመራር አባላትና ሠራተኞች ባንኩ በሚሠራባቸው የአገሪቱ ክፍሎች በሰፊው ያሳተፈና ንቅናቄ የፈጠረ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ መርሐ ግብሩ በማእከል ደረጃ ም/ፕሬዝዳንቶችን ባካተተ ኮሚቴ፣ በቀጣና እና በቅርንጫፍ የዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴና በልዩ ልዩ ኹነቶች ክትትል ኮሚቴ የሚመራ ስለነበር ወሩን ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በተሳካ ሁኔታ አክብረናል ማለት እችላለሁ፡፡ ለቀጣይ መሰል ዝግጅቶች ጥሩ ተሞክሮ ያገኘንበት ትልቅ አጋጣሚ ሆኖም ነው ያገኘነው፡፡ በተጨማሪም መድረኩ የተዘጋጀው የባንካችን ስኬት በደንበኞቻችን ላይ ለመመሥረቱ ዕውቅና ለመስጠትና ምስጋና ለማቅረብ በመሆኑ ይህንኑ ማድረግ ችለናል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ ከደንበኞቻችን ጋር ባደረግነው የፊት ለፊት የመድረክ ውይይት ገንቢ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ግብአቶችን ማግኘት ችለናል፡፡

ከዚህ አኳያ ከየዘርፉ ደንበኞች ጋር ባካሄድናቸው የፊት ለፊት የመድረክ ውይይቶች በምርትና አገልግሎት አቅርቦት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በአሠራር ሂደቶች፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ማሳለጥ እንዲሁም ለደንበኞች በሚሰጡ

መረጃዎች ተደራሽነት ረገድ ያሉብንን ክፍተቶች ለይተናል። ባጠቃላይ ለደንበኞቻችን ግልጽ መደረግ የሚገባቸውን ጉዳዮች መድረኮቹን በመጠቀም ስላስተላለፍን ዝግጅቶቹ ዓላማዎቻቸውን አሳክተዋል የሚል እምነት ነው ያለኝ።

**ዐውደ ንዋይ፡-** በደንበኞች አገልግሎት ወር ከደንበኞች ከተገኙ ግብአቶች በመነሣት ሊከናወኑ የታቀዱ የአሠራር ማሻሻያ ተግባራት ካሉ ቢጠቅሱልን?

**አቶ ኃይለየሱስ፡-** ባንካችን ርእዩን እውን ለማድረግ ዓለም አቀፋዊ እና አገራዊ ለውጦችን ታሳቢ ያደረገ የስትራቴጂ ክለሳ ሥራ በተሳካ ሁኔታ አጠናቅቆ ወደ ተግባር ለመግባት የተጠናከረ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ ከደንበኞች ጋር ባደረግነው ውይይት ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከአሠራር ሂደቶች እንዲሁም ከቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ማሳለጥ ጋር በተያያዘ ያሉብንን ክፍተቶች መለየት ችለናል።

በመሆኑም፣ ማሻሻያዎች በተከለሰው የ5 ዓመት መሪ ዕቅድም ሆነ በማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎቹ እንዲካተቱና በትኩረት እንዲሠራባቸው አቅጣጫ ተይዟል፡፡ ከነዚህ ውስጥ በዋነኛነት ትኩረት የተሰጠው ደንበኛን ማእከል ያደረገ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ በተጨማሪም የደንበኞች ቅሬታ አቀባበልና አፈታት ሥርዓት ከአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ሥራ ጋር ተነጥሎ ስለማይታይ፣ ባንካችን ከደንበኞች በተለያዩ መንገዶች ለሚቀበላቸው አስተያየቶችና ቅሬታዎች በልዩ ትኩረት ምላሽ ይሰጣል፡፡ ከዚህ ባሻገር በቀጣይ ከቴክኖሎጂና ከአሠራር ማሻሻያዎች ጋር የተያያዙ ለውጦች ይደረጋሉ። እነሱም አገልግሎታችንን የበለጠ የሚያዘምኑና የደንበኛን እርካታ የሚጨምሩ እንደሚሆኑ ሙሉ እምነት አለኝ።

**ዐውደ ንዋይ፡-** “የላቀ አገልግሎት፣ ደስተኛ ደንበኛ” የሚለውን መሪ ቃል እውን በማድረግ ረገድ የባንኩ አመራር ድርሻውን እንዲወጣ ለማድረግ ምን እየተሠራ ነው?

**አቶ ኃይለየሱስ፡-**

- የባንኩ አመራር ለአገልግሎት አሰጣጥ ልዩ ትኩረት ይሰጥ ዘንድ ለአመራር አካላት የደንበኞችን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ እና የመሪነት ሚናቸውን እንዲጫወቱ የሚያስችሉ ሥልጠናዎችን መስጠት የቅድሚያ ቅድሚያ ተሰጥቶት እየተሠራበት ይገኛል።
- በተዋረድ ያለው አመራር የትኛውንም ዓይነት የደንበኛ ጉዳይ ለይደር እንዳይተው እና በተቻለ ፍጥነት እንዲፈታ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ ይህን የሚከታተልና የሚያስፈጽም በተዋረድ ባሉ የሥራ ሓላፊዎች የሚመራ የደንበኞች ጉዳይ መፍትሔ ሰጪ ኮሚቴም ተቋቁሞ ለደንበኞች ጉዳይ መፍትሔ እየሰጠ ይገኛል፡፡
- የአመራሩ አፈጻጸም ከደንበኞች እርካታ ጋር በተያያዘ በመደበኛነት ይገመገማል፤ ከግምገማው በመነሣትም አመራሩ የአገልግሎት ደረጃዎችን በማሻሻል ረገድ ያለው አስተዋፅኦ እስከምን ድረስ ነው የሚለውን ማየት ተችሏል።
- የደንበኞችን እርካታ በማሳደግ ረገድ የላቀ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የአመራር አባላት የሚሸለሙበትና ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸው ተጠያቂ የሚሆኑበት አሠራር ይተገበራል።
- ባንኩ የደንበኞች አገልግሎት ጥራትን ለማረጋገጥ ግልጽ የሆኑ የአገልግሎት ደረጃዎችንና መመሪያዎችን በማውጣት አመራሩ እነዚህን መመሪያዎች እንዲተገብር ያደርጋል።

**ዐውደ ንዋይ፡-** ከደንበኞች አገልግሎት ወር መሪ ቃል ጋር በተያያዘ ከባንኩ ደንበኞች ጋር በአካልም ሆነ በሌላ መንገድ የሚገናኙ ሠራተኞችን ይበልጥ ለማትጋት ምን ታቅዷል?

**አቶ ኃይለየሱስ፡-** የባንካችን ሠራተኞች ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት የቴክኒክ እና ከባንኩ አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ ዕውቀቶች እንዲሁም የደንበኛ አቀባበልና የተግባቦት ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ ከደንበኞች በተገኙ ግብአቶች መሠረት በደንበኛ መስተንግዶ፣ በሥነ ምግባር እንዲሁም ለደንበኞች ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ፈጥኖ ምላሽ በመስጠት ረገድ የታዩ ክፍተቶችን ለመድፈን የደንበኛ አቀባበል እና የተግባቦት ክህሎቶችን ለማበልጸግ በሚያስችሉ የዐቅም ግንባታ ተግባራት ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል። ሌላው ዕቅድ የደንበኛ አገልግሎት እርካታን ለማምጣት የሚያስችሉ ተግባራትን መለየትና ለእነዚህ ተግባራት መለኪያ በማዘጋጀት ከሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም እና የማትጊያ ሥርዓታችን ጋር ማስተሳሰር ነው።

**ዐውደ ንዋይ፡-** ባንካችን የሚሰጠውን ሁለገብ የዲጂታል ባንክ አገልግሎት ለደንበኞች አመቺ፣ ቀላልና ተደራሽ ከማድረግ አንጻርስ ምን እየተሠራ ነው?

**አቶ ኃይለየሱስ፡-** ባሁኑ ወቅት የባንክ ኢንዱስትሪው በደረሰበት የቴክኖሎጂ እና የአሠራር የእድገት ደረጃ አገልግሎቶች በዲጂታል አማራጮች እየቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ይህም ደንበኞችን በያሉበት ቦታ ሆነው ወደ ባንክ መምጣት ሳያስፈልጋቸው አገልግሎቶቹን ማግኘት ያስችላቸዋል ማለት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የዲጂታል ባንክ አገልግሎትን ለደንበኞች አመቺ፣ ቀላል እና ተደራሽ ለማድረግ መጀመሪያ በዚህ ረገድ የሚታዩ ክፍተቶችን መለየት ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ። ከዚህ አንጻር አንዱ ችግር በደንበኞች በኩል የሚስተዋል የአጠቃቀምና የግንዛቤ ማነስ ነው። ሌላው ደግሞ ስለ ዲጂታል ባንክ ደኅንነትና አስተማማኝነት የተሳሳቱ አመለካከቶች ወይም ጥርጣሬዎች መኖር ነው። በመሆኑም እነዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ ደንበኞችን ስለ ዲጂታል የባንክ አገልግሎቶች ግልጽ፣ ቀላል እና አሳታፊ በሆነ ግንኙነት ማስተማር ስለሚገባ በዚህ ላይ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

በመከናወን ላይ ካሉ ሥራዎች መካከል አንዱ ደንበኞች የዲጂታል ባንክ አገልግሎቶችን ለመጠቀም ይበረታቱ ዘንድ

ለደንበኞች አገልግሎት ነክ ምርጫዎች፣ ባሕርያት እና ፍላጎቶች ግላዊነትን ማላበስ (personalized services) ነው። ግላዊነት ደንበኞችን አገልግሎት ሰጪው ለእነሱ ተሞክሮ እና እርካታ ዋጋ እንደሰጠ እንዲሁም እንደተረዳቸው እንዲሰማቸው ሊያደርግ ይችላል። ሌላው ደግሞ ደንበኞች የዲጂታል የባንክ አገልግሎቶችን እንዲጠቀሙ ለማበረታታት የምዝገባ፣ የማረጋገጫ፣ የመለያ ማረጋገጫ፣ የግብይት እና የመሳሰሉ ሂደቶችን ማቅለል ነው። ቀለል ያሉ ሂደቶች የደንበኞችን ብስጭት፣ ግራ መጋባት እና ማመንታት ሊቀንሱ እንዲሁም በራስ መተማመናቸውን እና ምቾታቸውን ሊጨምሩ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል።

ዐውደ ንዋይ:- የደንበኞችን ፍላጐት የማርካት ዓላማ በሚፈለገው ደረጃ ስለመሳካቱ ቀጣይነት ያለው ክትትል እና ግምገማ ከማድረግ አንጻር ምን እየተሠራ ነው?

አቶ ኃይለየሱስ:- የደንበኞች እርካታ ያለበትን ደረጃ መረዳት የሚቻለው በዋናነት ከደንበኞች ግብረ መልስ በመነሣት ስለሆነ ባንካችን ከደንበኞች በተለያዩ መንገዶች ለሚደርሱት አስተያየቶችና ቅሬታዎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል። በደንበኞች ግብረ መልስ ተመሥርቶ የማሻሻያ እርምጃዎችን መውሰድ ይቻል ዘንድ በዋናነት ግልጽ ግቦችን እና የሥራ አፈጻጸም መለኪያዎችን (KPIs) የመወሰን፣ ጠንካራ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን የማበልጸግ፣ መረጃን በየጊዜው ተከታትሎ አዝማሚያዎችን የመተንተን እና መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለመለየት ጥልቅ ግምገማዎችን የማካሄድ ተግባራት ይከናወናሉ። ተጨባጭ እርምጃዎችን እየወሰዱ እና ለውጦችን እየተገበሩ ደንበኛ ተኮር ድርጅታዊ ባህልን የማዳበር ተግባርም ይከናወናል።

ዐውደ ንዋይ:- የደንበኞች አገልግሎት ወርን ወደፊት በቋሚነት ማክበር የባንካችንን መልካም ገጽታ በማስተዋወቅ እና አዳዲስ ደንበኞችን በመሳብ ረገድ ምን ያህል ውጤታማ ያደርጋል ብለው ያምናሉ?

አቶ ኃይለየሱስ:- የደንበኞች አገልግሎት ወርን በተለያዩ ዝግጅቶች እና ለደንበኞች ልዩ ትኩረት በመስጠት ማክበር በራሱ የባንካችንን አዎንታዊ ገጽታ እንደሚያጎላ ነው የሚታመነው፡፡ ለደንበኞች አገልግሎት ልዩ ትኩረት መስጠታችን ከነባር ደንበኞቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት አጠናክሮ ያስቀጥለዋል፡፡ የደንበኞች አገልግሎት ወርን ስናከብር ያዩ ሰዎች ስለ ባንኩ የበለጠ ለማወቅ እና አገልግሎቶቹን ለመጠቀም ፍላጎት ስለሚያድርባቸው መርሐ ግብሩ አዳዲስ ደንበኞችን ወደ ባንካችን በመሳብ ረገድም ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ነው የምናምነው። መልካም ስማችንን ከመናኘት ባለፈ አዳዲስ ደንበኞችን በመሳብ የረጅም ጊዜ እድገታችንን ያረጋግጣል። ይህን ዕድል በአግባቡ መጠቀም የባንካችንን ተወዳዳሪነት በእጅጉ ያሳድጋል ባይ ነኝ።

ዐውደ ንዋይ:- በዚህ አጋጣሚ ለባንካችን ሠራተኞች እና




ደንበኞች ሊያስተላልፉ የሚፈልጉት መልእክት ካለ ቢነግሩን?

አቶ ኃይለየሱስ:- ለመላው የባንካችን የሥራ አመራር አባላትና ሠራተኞች ማስገንዘብ የምፈልገው በመጀመሪያ ባንካችን በቀጣይ በኢንዱስትሪው የውድድር መድረክ አሸናፊ ሆኖ መውጣት የሚችለው በደንበኞች ዘንድ ባለው ተመራጭነት ብቻ መሆኑን ተረድተን ዋና ግባችን ይህን ታሳቢ ያደረገ መሆን እንዳለበት ነው። በመቀጠልም በባንካችን ማኅበረሰብ ዘንድ አሁን እየተስተዋለ ያለው ለደንበኞች የተሻለ አገልግሎት የመስጠት ተነሣሽነት ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ለማሳሰብ እወዳለሁ።

ደንበኞቻችን የህልውናችን መሠረት መሆናቸውን ለአፍታም ቢሆን አለመዘንጋት፣ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ የአንድ ሰሞን ዝግጅት ብቻ እንዳልሆነ በመረዳት ቀጣይነት ያለው ደንበኛ ተኮር የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ባህላችንን ማሻሻልና የደንበኞችን እርካታ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በየደረጃው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባናል። በዚህ መልኩ ትኩረት ሰጥተን ከሠራን ባንካችን ወደፊት በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ መሪ ሆኖ በአርአያነት የሚጠቀስ ተቋም እንደሚሆን ሙሉ እምነት አለኝ።

ለደንበኞቻችን ደግሞ ባንካችን የላቀ አገልግሎት በመስጠት እናንተን ለማርካት ተግቶ እንደሚሠራ በባንኩ ስም አረጋግጣለሁ። የአገልግሎት አሰጣጣችን መስታወት በመሆናችሁ እንዲሁም የምታቀርቧቸው አስተያየቶች እና ቅሬታዎች ለጥንካሬያችን ግብአት በመሆናቸው ቅሬታዎቻችሁን ባግባቡ እየፈታን ለጋራ እድገት አብረን እንድንሠራ በዚህ አጋጣሚ በባንኩ ስም ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። አመሰግናለሁ፡፡

ዐውደ ንዋይ:- እኛም እናመሰግናለን!

# መዝናኛ

## ከቀድሞ ማስታወቂያዎቻችን አንዱ

አንድ በዕድሜ የገፉ ሰው ባንክ ገብተው የ500 ዶላር ብድር ጠየቁ። የባንኩ ሠራተኛም የብድር ቅጾቹን መሙላት ጀመረ.።

• በዚህ ገንዘብ ምን ሊያደርጉበት ነው?
• የሠራሁትን ጌጣጌጥ ለመሸጥ ወደ ከተማ እሄዳለሁ።
• ለብድሩ ማስያዣ የሚሆን ነገር አለዎት?
• እኔ አላውቅም፤ ማስያዣ ምንድን ነው?
• ማስያዣ የሚባለው ዋጋ ያለው እና የብድር ወጪን ሊሸፍን የሚችል ነገር ነው። መኪና አለዎ?
• አዎ። እ.ኤ.አ. በ1949 የተመረተ የጭነት መኪና።
• አይሆንም። ምናልባት የእንስሳት እርባታ ይኖርዎት ይሆን?
• አዎ፤ ፈረስ አለኝ.።
• ዕድሜው ስንት ነው?
• እኔ አላውቅም፤ ምክንያቱም ጥርስ የለውም።

መጨረሻ ላይ የብድሩ ቅጾች ተሞልተው ለሰውየው 500 ዶላር ተሰጣቸው።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ሰውዬው እንደገና የታሸገ ገንዘብ ይዘው ወደ ባንኩ መጡ። የባንኩን ድርሻ ቆጥረው ከቀነሱ በኋላ፣ ሌላውን ደበቁና ከሠራተኛው ጋር መነጋገር ጀመሩ።

• በሌላው ገንዘብ ምን ሊያደርጉበት ነው?
• ቤቴ ወስጄ አስቀምጠዋለሁ።
• እኛ ባንክ ዘንድ ተቀማጭ ማድረግ ይችላሉ እኮ።
• ተቀማጭ ማድረግ ማለት ምንድን ነው?
• ገንዘቡን እኛ እንድንይዝልዎ ለባንካችን መስጠት ነው። በሌላ ጊዜ ገንዘብ ሲፈልጉ ሊወስዱት ይችላሉ።
• ባንካችሁ ለገንዘቡ የሚሰጠኝ ማስያዣ አለ?

*መነሻ ምንጭ፡-* https://www.inspirationalstories.eu/funny-story-about-money/#:~:text=An%20old%20man,for%20the%20money%3F




ዋስይሁን ፈቃደ

# ከፎቶ ማኅደር

አሊቃ በላይ




ኢ.ን.ባ. ለባቡል ኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ ሲያደርግ





ኮሜርሻል ኖሚኒስ ሓላ/ የተ/የግ/ ማኅበር ለመቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማእከል ድጋፍ ሲያደርግ



የደንበኞች አገልግሎት ወር የመክፈቻ መርሐ ግብር ስብሰባ



ከየሁሉ የብድር እና ቁጠባ የኅብረት ሥራ ማኅበር ጋር የመግባቢያ ስምምነት ሲፈረም



በደንበኞች አገልግሎት ወር የተደረገ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ



በባሌ ጎባ ከተማ ከሚገኙ ደንበኞች ጋር ውይይት ሲደረግ



በመቀሌ ከተማ ከሚገኙ ደንበኞች ጋር ውይይት ሲደረግ



የኢ.ን.ባ. የ2017 የበጀት ዓመት የ2ኛ መንፈቅ ዓመት አፈጻጸም
የተገመገመበት ጉባኤ



በባሌ ሮቤ ከተማ የተካሄደ ሶደቃ



ኢ.ን.ባ.ን ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ ሠራተኞች የተሸለሙበት መድረክ


ሲቢኢ ኑር
CBE NOOR
ዘካዎን ለመስጠት እኛ አለንልዎት!
ዘካ ተቀማጭ ሂሳብ
ZAKAT DEPOSIT ACCOUNT
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia